የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር

# አዲስ ነጋሪ ጋዜጣ

# ADDIS NEGARI GAZETA

**OF THE CITY GOVERNMENT OF ADDIS ABABA**

ሁለተኛ አመት ቁጥር ፰
አዲስ አበባ መስከረም ፳፰ ቀን ፪ ሺ ፩ ዓ.ም

በአዲስ አበባ ከተማ
ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

2nd Year No.8
ADDIS ABABA 8th October 2008

ማውጫ
አዋጅ ቁጥር ፮/፲፱፻፺፫
የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የአማካሪ
ምክር ቤት ማቋቋሚያ አ..............................ገጽ ፩

## አዋጅ ቁጥር ፮/፲፱፻፺፫
## የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የአማካሪ
## ምክር ቤት ማቋቋሚያ አዋጅ

ጊዜያዊው የከተማው አስተዳደር ሲቋቋም ቀድሞ የነበሩት ምክር ቤቶች የፈረሱ ስለሆነ ለቀጣዩ የከተማው አስተዳደር የሕዝብ ምርጫ ነዋሪው ልምድ የሚቀስምበት መድረክ መፍጠር አስፈላጊ በመሆኑ፤

በከተማው መልካም አስተዳደር እና የዴሞክራሲ ግንባታ ፅኑ መሠረት ሊይዝ የሚችለው በሂደቱ ነዋሪው በንቃት ሲሳተፍ በመሆኑ፤

የከተማው ልማት ሊረጋገጥ የሚችለው እና ነዋሪውም የልማቱ ተጠቃሚ የሚሆነው ነዋሪው በባለቤትነት መንፈስ ሲሳተፍ በመሆኑ፤

ለከተማው ነዋሪ የሚቀርቡ አገልግሎቶች ዓይነት፣ መጠንና ጥራት አስተማማኝ ሊሆን የሚችለው በነዋሪው ቀጥተኛ ተሳትፎ በመሆኑ፣

የአዲስ አበባ ከተማ ጊዜያዊ አስተዳደር በተሸሻለው የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ቻርተር አዋጅ ቁጥር ፫፻፲፩/፲፱፻፺፫ አንቀጽ ፲፫/፩/ረ/ እና አንቀጽ ፷፮ (፪) እና ፷፮(፫)፩ (መ) መሠረት ይህንን አዋጅ አውጥቷል፡፡

### ክፍል አንድ
### ጠቅላላ

**፩. አጭር ርዕስ**

ይህ አዋጅ “የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የአማካሪ ምክር ቤት ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር ፮/፲፱፻፺፫ ዓ.ም.” ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

Proclamation No. 6/2003
The Addis Ababa City Government Advisory Council
Establishment Proclamation

## PROCLAMATION NO. 6/2003
## THE ADDIS ABABA CITY GOVERNMENT ADVISORY COUNCIL ESTABLISHMENT PROCLAMATION

WHEREAS, it has become necessary to create a forum for the residents of the city to gain experience for the next election as the former councils of the city have been dissolved upon the establishement of the provisional city Government;

WHEREAS, active participation of the residents is necessary for the firm foundation and prevalence of good governance and democratic order of the city;

WHEREAS, development of the city can be ensured and its residents benefit from it when residents participate in such development with the spirit of ownership;

WHEREAS, development of the city can be ensured and its residents benefit from it when residents participate in such development with the spirit of ownership;

WHEREAS, direct participation of the residents of the city is necessary for reliable provision of services in kind, quality and quantity to the residents;

NOW, THEREFORE, in accordance with Article 13/1/F/ and 66(2) and 66(3) (d) of the Addis Ababa City Government Revised Charter Proclamation No. 311/2003 it is proclaimed as follows:

PART ONE
General

**1. Short Title**

This Proclamation may be cited as the “Addis Ababa City ... clamation No.

ያንዱ ዋጋ 7.60
Unit price

አዲስ ነጋሪ ጋዜጣ ፖ.ሣ.ቁ ፳፬፻፵፭
Addis Negari Gazeta P.O.Box 2445

፪. ትርጓሜ
በዚህ አዋጅ ውስጥ፤
፩. "ከተማ" ማለት የአዲስ አበባ ከተማ ነው፤
፪."የከተማ አስተዳደር" ማለት የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ነው፤
፫. "የአማካሪ ምክር ቤት" ማለት እንደአግባብነቱ የከተማ ምክር ቤት፣ የክፍለ ከተማ ምክር ቤት፣ የቀበሌ ምክር ቤት ነው፡፡

ክፍል ሁለት
ማቋቋም፣ ጽሕፈት ቤት፣ ከተማ፣ የክፍለ ከተማ፣ የቀበሌ፣ አማካሪ ምክር ቤት አባላትና አባልነት

፫. የአማካሪ ምክር ቤቶች መቋቋም
በዚህ አዋጅ መሠረት የሚከተሉት ምክር ቤቶች ተቋቁመዋል፤
፩. የከተማው አስተዳደር የአማካሪ ምክር ቤት፤
፪. የክፍለ ከተማ የአማካሪ ምክር ቤት፤
፫. የቀበሌ የአማካሪ ምክር ቤት፡፡

፬. የጽህፈት ቤት
የከንቲባው ጽሕፈት ቤት፣ የክፍለ ከተማው ዋና ሥራ አስፈፃሚ ጽሕፈት ቤት፣ የቀበሌ ዋና ሥራ አስፈፃሚ ጽሕፈት ቤት እንደ ቅደም ተከተሉ የየዐማካሪ ምክር ቤቱ ጽሕፈት ቤቶች ሆነው ይሰራል፡፡

፭. የከተማ አማካሪ ምክር ቤት አባላት
፩. የከተማ አማካሪ ምክር ቤት የሚከተሉት አባላት ይኖሩታል፤
፩. የከተማ ከንቲባ ............................. ሰብሳቢ
፪. የካቢኔ አባላት .............................. አባል
፫. የከተማው ሥራ አስኪያጅ.................... አባል
፬. የከተማው ምክትል ሥራ አስኪያጅ.......... አባል
፭. ምክትል የቢሮ ኃላፊዎች .................... አባሎች
፮. የከተማው አስተዳደር መሥሪያ ቤቶች ኃላፊዎች ................................................. አባሎች
፯. የክፍለ ከተማ ዋና ሥራ አስፈፃሚ፣ ምክትል ዋና ሥራ አስፈፃሚ እና ቋሚ ኮሚቴ.............አባሎች
፰. ከየቀበሌው ሁለት የነዋሪዎች ተወካይ...... አባሎች
፱. የቀበሌ ቋሚ ኮሚቴ.......................... አባል
፲. የከተማው ሴቶች ማህበር ተወካይ.......... አባል
፲፩. የከተማው ወጣቶች ማህበር ተወካይ........ አባል
፲፪. የሠራተኛ ማህበር ተወካይ.................. አባል
፲፫. የአዲስ አበባ ንግድ ምክር ቤት ተወካይ.....አባል
፲፬. የኢትዮጵያ አምራች ኢንዱስትሪ ባለሀብቶች ማህበር ተወካይ................................ አባል
፲፭. መምህራን ማህበር ተወካይ................. አባል
፲፮. የሙያ ማህበራት ተወካይ.................... አባል
፲፯. የኢትዮጵያ አርበኞች ማህበር ተወካይ.......አባል
፲፰. የሲቪል ህብረተሰብ ማህበራት ተወካይ.....አባል
፲፱. ዩንቨርስቲ እና ከፍተኛ የትምህርት ተቋማት ተወካይ......................................... አባል
፳. የጤና ባለሙያዎች ማህበር ተወካይ........ አባል
፳፩. መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ተወካይ...አባል
፪. የከተማ አማካሪ ክር ቤት ተወካዮች ቁጥር ከስድስት መቶ አስከ ሰባት መቶ የሚደርስ ሲሆን ዝርዝሩ በአባሪ ቁጥር ፩ የተመለከተው ይሆናል፡፡

፮. የክፍለ ከተማ አማካሪ ምክር ቤት አባላት
፩. የክፍለ ከተማ አማካሪ ምክር ቤት የሚከተሉት አባላት ይኖሩታል፤

**2. Definitions**
In this Proclamation;
1. "City means the Addis Ababa City
2. "City Government" means the Addis Ababa City Government;
3. "Advisor Council" means City Sub-City or Qebele Advisory Council as appropriate.

PART TWO
Establishment. Office, members of the Advisory Council of the City Government, Sub-City, qebele and Membershio.

**3. Establishment of Advisory Councils**
The following Councils shall be established by this proclamation;
1. The Advisory Council of City Government.
2. The Advisory Council of Sub-City.
3. The Advisory Council of Qebele.

**4. Office**
The Office of the Mayor, the Office a of the Chief Executive of Sub-City and the office of the chief Executive of Qebele shall respectively serve as the offices of the Advisory Councils.

**5. Members Of Advisory Council of the City Government**
1. The Advisory Council of the City Government shall have the following members:
1. The Mayor……………………………………….chairperson
2. City Cabinet Members………………………….Member
3. The City manager……………………………….Member
4. The Deputy City Manager……………………… Member
5. The Deputy heads of Bureaux………………… Members
6. The Heads of Organs of the City Government ….Members
7. The sub-City Executive, Deputy Chief Executive and standing committee…………………………… ……………Members
8. Two representatives of residents from each Qebele…Members
9. The Qebbele Standing Committee Reperesentative of... Member
10. Representative of the city Association of women ……Member
11. Representative of the city Association of youth.... …..Member
12. Representative of the Labour Union Association.......Member
13. Representative of the Addis Ababa Chamber of Commerce …………………………………………………. Member
14. Representative of the Ethiopian Manufacturing Industries Owners` Association ……………………………. ….Member
15. Representative of the Association of Teachere…. …Member
16. Representative of the propffessionals` Association ..Member
17. Representative of the ethipopian patrotic Association ..Member
18. Representative of the Civil Societies………………..Member
19. Representative of the Universty and Inistitution of Higher education …………………………………………..Member
20. Representative of the Health professional`s Association …………………………………………………..Member
21. Representative of the Non-Governmental Organizations …………………………………………………..Member

2. The total number of members of the city advisory Council shall range from six hundred to seven hundreds and the details are provided under Annex 1 thereof.

**6. Members Of Sub-City Advisory Council**
1. The Sub-city Advisory Council shall have the following members;

፩. የክፍለ ከተማው ዋና ሥራ አስፈፃሚ………… ሰብሳቢ
፪. የክፍለ ከተማው ቋሚ ኮሚቴ…………………….. አባል
፫. ከየቀበሌው ሃያ የነዋሪ ተወካዮች………………… አባል
፬. የቀበሌ ቋሚ ኮሚቴዎች…………………..…… አባል
፭. የክፍለ ከተማው መሥሪያ ቤቶች ኃላፊዎች…… አባል
፮. የክፍለ ከተማው የሴቶች ማህበር ተወካይ……….. አባል
፯. የክፍለ ከተማው ወጣቶች ማህበር ተወካይ……… አባል
፰. የክፍለ ከተማው መምህራን ማህበር ተወካይ...... አባል
፱. የአዲስ አበባ ንግድ ምክር ቤት ተወካይ…….....አባል
፲. የሲቪል ህብረተሰብ ማህበራት ተወካይ……..... አባል
፲፩. መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ተወካይ……… አባል

፪. የክፍለ ከተማ አማካሪ ምክር ቤት አባላት ቁጥር ከአምስት መቶ እስከ ሰባት መቶ የሚደርስ ሲሆን ዝርዝሩ በአባሪ ቁጥር ፪ የተመለከተው ይሆናል፡፡

፯. የቀበሌ አማካሪ ምክር ቤት አባላት

፩. የቀበሌ አማካሪ ምክር ቤት የሚከተሉት አባላት ይኖሩታል፣
፩. የቀበሌው ዋና ሥራ አስፈጻሚ……………..ሰብሳቢ
፪. የቀበሌ ቋሚ ኮሚቴ………………………….አባል
፫. የቀበሌ ነዋሪ ተወካዮች……………………..አባል
፬. ሴቶች ማህበር ተወካዮች……………………..አባል
፭. የወጣቶች ማህበር ተወካይ…………………..አባል
፮. መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ተወካይ……አባል
፯. የመምህራን ማህበር ተወካዮች………………..አባል
፰. የህክምና ባለሙያዎች ማህበር ተወካዮች…….አባል
፱. የቀበሌ የትምህርት ዴስክ……………..…….አባል
፲. የቀበሌ የትምህርት አመራር ተወካዮች..…….አባል
፲፩. የሲቪል ህብረተሰብ ማህበራት ተወካይ..……አባል
፲፪. የአካባቢ ልማት ኮሚቴ……………...……..አባል
፲፫. የአካባቢ ልማት ኮሚቴ……………..……..አባል
፲፬. የእድሮች ተወካዮች………………..………..አባል

፪. የቀበሌ አማካሪ ምክር ቤት አባላት ቁጥር ከአምስት መቶ እስከ ስድስት መቶ ሆኖ ዝርዝሩ በአባሪ ቁጥር ፫ የተመለከተው ይሆናል፡፡

፰. አባልነት

፩. ከየቀበሌው ለከተማ ምክር ቤት እና ለክፍለ ከተማ ምክር ቤት የተወከሉ ነዋሪዎች፣ በተደራቢነት በተዋረድ በየሚመለከታቸው ክፍለ ከተማ እና ቀበሌ ምክር ቤት ይሳተፋሉ፡፡
፪. በማንኛውም የአማካሪ ምክር ቤት ከሚገኙ አባላት ውስጥ ሁለት ሶስተኛው የነዋሪው ተወካዮች ይሆናል፡፡

ክፍል ሦስት

የአማካሪ ምክር ቤት ስልጣንና ተግባር የምክር በቤቱ ሰብሳቢ፣ ፀሐፊ፣ የምክር ቤቱ ኮሚቴዎች ሰብሳቢ ሥነ ሥርዓትና ቃለ ጉባኤ

፱. የአማካሪ ምክር ቤት ሥልጣንና ተግባር፣

፩. ማንኛውም በዚህ አዋጅ መሠረት የተቋቋመ ምክር ቤት የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፣
፩. በከተማው አስተዳደር ዕቅዶችና አፈፃፀማቸው ላይ ይመክራል አፈፃፀማቸውንም ይከታተላል፡፡
፪. በከተማው አስተዳር በጀት ቁጠባዊ አጠቃቀም ላይ ይመክራል፡፡
፫. የከተማው አስተዳር በሚያወጣቸው ህጎች፣ ደንቦችና መመሪያዎች ላይ ምክር ይሰጣል፣
፬. በከተማው ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ልማት ዕቅድ ዝግጅት ላይ ይመክራል፣
፭. በከተማው ፀጥታ ጉዳዮች ላይ ይመክራል፣
፮. በከተማው አስተዳደር ጉዳዮች ላይ ምክር ይሰጣል፣
፯. በህዝብና በከተማው አስተዳደር በጋራ ለሚከናወኑ ፕሮጀክቶች ማስፈፀሚያ የሚውል የሕዝብ መዋጮ የሚሰበሰብበትን ሁኔታ ያመቻቻል፡፡

1. Chief Excutive of Sub-city………………….chairperson
2. Standinge Committee of Sub-City…………...Member
3. Twenty representatives of residents from each Qebele ………………..……………………………………...Member
4. Qebele standing committee…..……………… Member
5. Heads of organs of Sub-city………………… Members
6. Representatives of the Association of women of the Sub-city..……………………………………Members
7. Reperesentative of the Association of Youth of the Sub-City……………………………………......Members
8. Reperesentative of the Association of Teacher of the Sub-City…………………………………. Members
9. Reperesentative of the Addis Ababa chamber of Commerce…….. ……………………………. Member
10. Reperesentative of the Civil Societies………. Member
11. Reperesentative of the Non-Government organizations -Member

2. the total numbers of Sub-City Advisory Council shall range from five hundered to seven hundered and the details are provided under Annex 2 thereof..

**7. Members of Qebele Advisory Council**

1. The Qebele Advisory Council shall have the following members:
   1. Chief Excutive of the Qebele ……………………………….chairperson
   2. Standinge Committee of the Qebele …………..................Member
   3. Qebele residents` representatives……………..----------------Member
   4. Reperesentative of the Association of women......................Member
   5. Reperesentative of the Association of youth…......................Member
   6. Reperesentative of the Non-Governmental organization……-Member
   7. Reperesentative of the Association of Teachers……………..Member
   8. Reperesentative of the Health professionals Association…….Member
   9. Qebele Education desk……………………….......................Member
   10. Qebele Education Management representatives....................Member
   11. Reperesentative of the Civil Associations.............................Member
   12. Qebele Development Committee ….………….....................Member
   13. Local Development Associastions……………......................Member
   14. "Edire" representatives…………………..…………………. Members
2. The total number of members or Qebele Advisory Council shall range from five hundred to six hundred the details are provided under Annex 3 thereof.

**8. Membership**

1. Residents represented from each Qebele in the city Advisoruy Council and Sub-City Advisory Council shall in Addition participate in the Sub-City Advisory Council and Qebele Advisory Council respectively.
2. Two-third of the members of any Advisory Council shall be representatives of the residents.

PART THREE

Powers and functions of chairperson, secretary, committees, rules of procedures of the Meening and minutes of the Advisorty coicil

**9. powers and Functions of the Advisory Council**

1. any Advisory Council established by this proclamation shall have the following powers and functions to:
   1. discuss the plan and implementation of the city Government, supervise the implementation of same;
   2. Discuss the economical utilization of the budget of the City Governement
   3. Gve advice on proclamations, regulations and directives to be issued by the city government.
   4. Discuss on the preparation of the social and economic development plan of the city.
   5. Discuss on the security issues of the city;
   6. Give advice on the administrative issues of the City.
   7. Facilitate the connections of the contribution made by residents that would be utilized to the projects undertaken jointly by the city and the resedents.

፰. በህዝብና በከተማው አስተዳደር በጋራ የተሠሩ ፕሮጀክቶችን እንክብካቤ ይከተታል፡፡
፱. በከተማው ነዋሪና በከተማው አስተዳደር መካከል በልማት እና በአስተዳደር ረገድ የግንኙነት መድረክ በመሆን ያገለግላል፤
፲. የከተማው ነዋሪ በከተማው ልማትና መልካም አስተዳደር እንዲሰፍን ተደራጅቶ በፈቃደኝነት ሙሉ ተሳትፎ ስለሚያሳድጋቸው ሁኔታዎች ይመክራል፤ ስልቶችን ይነድፋል፤
፲፩. ለከተማው ነዋሪ የሚቀርቡ አገልግሎቶች ዓይነት መጠንና ጥራት ደረጃውን የጠበቀና ቀጣይነት ያለው መሆኑን ለማረጋገጥ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር ይመክራል፡፡

፪) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) ሥር የተዘረዘሩት ሥልጣንና ተግባራት እንደአግባብነቱ ለክፍለ ከተማና ለቀበሌ ምክር ቤቶች ተፈፃሚነት ይኖራቸዋል፡፡

፲. አማካሪ ምክር ቤቱ ሰብሳቢ

የምክር ቤት ሰብሳቢ በማይገኝበት በማንኛውም ጊዜ ምክትል ሰብሳቢ ተክቶ የሚሠራ መሆኑ እንደተጠበቀ ሆኖ አማካሪ ምክር ቤቱ ሰብሳቢ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፤

፩. የምክር ቤቱን ስብሰባዎች ይመራል፣ ምክር ቤቱን ይወክላል፣ ያስተባብራል፤
፪. በአማካሪ ምክር ቤቱ ስብሰባ ላይ ቀርበው ማብራሪያ የሚሰጡ የሥራ ኃላፊዎች፣ ባለሙያዎች፣ ወይም አግባብነት ያላቸው ግለሰቦች እንዲገኙ ይፈቅዳል፤
፫. የአማካሪ ምክር ቤቱን ፀሐፊ ይመድባል ይህንንም ለምክር ቤቱ ያሳውቃል፤
፬. አማካሪ ምክር ቤቱ የሚስማማባቸውን የምክር አስተያየቶች በሥራ ላይ መዋላቸውን ይከታተላል፡፡

፲፩. የአማካሪ ምክር ቤቱ ፀሐፊ

የአማካሪ ምክር ቤቱ ፀሐፊ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፤

፩. የአማካሪ ምክር ቤቱን ጽህፈት ቤት በኃላፊነት ይመራል፣
፪. በአማካሪ ምክር ቤቱ ጽህፈት ቤት ስም ከሌሎች አካላት ጋር ይፃፃፋል፤
፫. የአማካሪ ምክር ቤቱን የሥራ ፕሮግራምና የውይይት አጀንዳዎች በማዘጋጀት ረገድ ለምክር ቤቱ ሰብሳቢ ድጋፍ ይሰጣል.
፬. ቃለ ጉባኤዎች ይመዘግባል፣ ይይዛል፣
፭. ለአማካሪ ምክር ቤቱ የሚያስፈልጉት ቁሳቁሶች እንዲሟሉ ያደርጋል፡፡
፮. በአማካሪ ምክር ቤቱ ሰብሳቢ የሚሰጡትን ሌሎች ተግባሮች ያከናውናል፡፡

፲፪. የአማካሪ ምክር ቤት ኮሚቴዎች

፩. አማካሪ ምክር ቤት እንደአግባብነቱ ኮሚቴዎች ሊሰይም ይችላል፡፡
፪. የአማካሪው ምክር ቤት ኮሚቴዎች ምክር ቤቱና ለሰብሳቢው በፖሊስ ጉዳዮች ላይ የምክር አገልግሎት ይሰጣሉ፤ የአማካሪ ምክር ቤቱን አስተያየቶች አፈፃፀም ይከታተላሉ፣ ይገመግማሉ፡፡
፫. የኮሚቴዎች አሰራር አማካሪ ምክር ቤቱ በሚያወጣው ውስጥ ደንብ ይወሰናል፡፡

8. Follow up the care taken to projects under taken jointly by the city government and the resedents;
9. Service as a forum where residents of the City and the city government could discuss development and administrative matters;
10. Counsel and devise straregies whereby the residents of the City could organize themselves and increase their voulentary full participation in the realization of development and good governance;
11. Counsel with other concerned bodies to ensure that the type, quality and quantity of services delivered top the residents of the city are up standard and sutainable.

2. Powers and functions provided under sub-Article 1 of this Article shall be applicable to the sub-City and Qebele Advisory Councils as appropriate.

10. Chairperson of Advisory Council

Notwitshstanding that the vice Chair person shall act the same in the absence of the chairperson; the chairperson of Advisory Council shall have the following powers and functions to:

1. Preside the meeting of the council; reperesent and coordinate the activities of the council,
2. Permit the appearance of officials, professional and other appropriate individuals who present elaborations at the metting of the council,
3. Appoint the secretary of the Advisory Council and disclose same to the Council;
4. Follow up the implementation of recommendations of the Councuil.

11. Secretary of the Advisory Council

The secretary of the Advisory Council shall have the following powers and functions to;

1. Direct the office of the Advisory Council;
2. Correspond in the name of the Advisory Council;
3. Assist the chairperson in the preparation of agendas and work programs of the Advisory Council.
4. Record and give coustodial service for the minutues of the council
5. Make available facilities required by the Advisory Council.
6. Perform other functions assigned by the chairperson of the Advisory Council.

12. Committees of Advisory Council

1. The Advisory Council may assign Committees where appropriate.
2. The Committees of the Advisory Council shall deliberate the council and the chairperson on policy matters and follow up and evaluate the implementation of the recommendation of the Advisory council.
3. The manner and ways by which the Committees conduct their task shall be determined by internal regulations issued by the Advisory Council.

፲፫. የአማካሪ ምክር ቤት የስብሰባ ሥነ-ሥርዓት

፩. የከተማው እና የክፍለ ከተማ አማካሪ ምክር ቤቶች በየሦስት ወሩ አንድ ጊዜ የሚካሄድ መደበኛ ስብሰባ ሲኖራቸው የቀበሌ አማካሪ ምክር ቤት በሁለት ወር አንድ ግዜ የሚካሄድ መደበኛ ሲኖራቸው የቀበሌ አማካሪ ምክር ቤት በሁለት ወር አንድ ጊዜ የሚካሄድ መደበኛ ስብሰባ ይኖረዋል፤ እያንዳንዱ ምክር ቤት አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው አስቸኳይ ስብሰባ ሊኖረው ይችላል፤ ዝርዝሩ በምክር ቤቱ በሚወጣ የውስጥ ደንብ ይወሰናል፡፡

፪. ምልዓተ ጉባኤ የሚኖረው ከአባላት ከግማሽ በላይ ሲገኙ ይሆናል፡፡

፫. ምልዓተ ጉባኤ መኖሩ በምክር ቤቱ ፀሐፊ ሲረጋገጥ ሰብሳቢው የአማካሪ ምክር ቤቱ ሥራውን እንዲጀምር ያደርጋል፡፡

፬. አንድ አባል በሰብሳቢው ተፈቅዶለት በመናገር ላይ እያለ ሌላ አባል ሊያቋርጠው አይችልም፤ ሆኖም ውይይቱ ፈር ለቋል ወይም ሥነ ሥርዓት ተጓድሏል ብሎ ለማመልከት ወይም መረጃ ለመስጠት የሚጠይቅ አባል “ስለ ደንብ” ወይም “ስለ መረጃ” ሲል ሰብሳቢው ተራ ጠብቆ እንዲናገር ዕድል ይሰጠዋል፣ የደንብ ጥያቄ ቅድሚያ የሚሰጠው ሲሆን መረጃና ማብራሪያ እንደ ቅደም ተከተላቸው ይቀርባሉ፡፡

፭. አማካሪ ምክር ቤቱ የሚያስተላልፈው የምክር አስተያየት በተባበረ ድምፅ ይሆናል፤ ይህ ካልተቻለ የአብዛኛው ድምፅ አስተያየት እና የአማራጭ አስተያየት ይተላለፋል፡፡

፮. የአማካሪ ምክር ቤቱ አስተያየት በአባላቱ ተፈርሞበት በሰብሳቢው እንደአግባብነቱ ለከተማ፣ ለክፍለ ከተማው፣ ለቀበሌው ከፍተኛ የሥልጣን አካል ይቀርባል፡፡

፲፬. የአማካሪ ምክር ቤቱ ቃለ ጉባኤ

፩.የአማካሪ ምክር ቤቱ ቃለ ጉባኤ የሚከተሉትን ይይዛል፤

ሀ) የስብሰባውን ቦታ፣ ቀንና ሰዓት፣

ለ) በስብሰባው ላይ የተገኙትን አካላት ዝርዝር፤

ሐ) በስብሰባው ላይ ያልተገኙትን አባላት ዝርዝርና ያልተገኙበትን ምክንያት፣

መ) በስብሰባው ላይ የተገኙ ሌሎች ሰዎች ካሉ ስማቸውንና የተገኙበትን ምክንያት፤

ሠ) ለስብሰባው የቀረበውን አጀንዳ፤

ረ) ለውይይቱ የቀረበውን ጉዳይ በአጭሩ የሚገልፅ ጽሁፍ፤

ሰ) ስብሰባው የተፈፀመበትን ሁኔታና ሰዓት፤

ሸ) ቃለ ጉባኤው ከፀደቀ በኋላ በአማካሪ ምክር ቤቱ ሰብሳቢና ፀሐፊ መፈረም ይኖርበታል፡፡

## ክፍል አራት
## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

፪. ስብሰባው ለነዋሪና ለመገናኛ ብዙኃን ክፍት ይሆናል፡፡

፲፭. ውስጥ ደንብ የማውጣት ሥልጣን

የአማካሪ ምክር ቤት ለዚህ አዋጅ አፈፃፀም የውስጥ ደንብ ማውጣት ይችላል፡፡

፲፮. አዋጁ ስለሚፀናበት ጊዜ

ይህ አዋጅ ከግንቦት ፯ ቀን ፲፱፻፺፭ ዓ.ም ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

አዲስ አበባ
ግንቦት ፯ ቀን ፲፱፻፺፭ ዓ.ም
የአዲስ አበባ ከተማ ጊዜያዊ አስተዳደር

13. Rules of procedures of the Meeting of the Advisory Council

1. The city and the sub-city advisory council shall have a regeular meeting once in every three months and Qebele Advisory council shall have a regular meeting once in every two months; each council shall have extra ordinary meeting as may be necessary. Yhe details shall be determined by the internal regulations of the council,
2. There shall be a qorum where more than half of the members of the Council are present.
3. The Chairperson shall make the council commence its duties where the secretary of the advisory council confirms that there is a qorum.
4. There shall not be any interruption while a member of the Council is speaking by the permission of the chair person; however, a member that belives there is disorder in the meeting may intervenene by saying "point of order" or "about information", the chairperson shall give him a chance to speak in turn. Point of order shall be given prioriyty and information or explanations shall be given properity and information or explanations shall be presented in their order.
5. Recommendations of the council may be passed by consensus; failing that, by majority vote. The decending opinions shall also be recerded and transferred.
6. The opinion of the Advisory Council Shall be presented of the supreme organs of the city, sub-City and Zebele as appropriate by the Chairperson. Upon affixing the signature of the council members.

14. Minutes of the Advisory Council

1. The minutes of The Advisory Council shall contain the following:
   (a) Place, time and date of the meeting
   (b) List of members attending the meting,
   (c) List of members not present in the meting and reason for their absence;
   (d) Name of other persons attending the metting and reasons for their presence;
   (e) Agenda submitted to the metting;
   (f) Brief memorandum explaning the issues presented for discussion;
   (g) The time and the manner in which the metting is concluded.
   (h) The minute shall be signed by the chairperson and the secretary of the Advisory Council after its approval.
2. The meeting shall be open to the residents of the city and the midia.

## PART FOUR
## Miscellaneais Provisions

15. Power to issue Rules of procedure

The Advisory council may issue Rules of procedure for the implementation of thisproclamation.

16. Effective Date

This proclamation shall come in to forces as of 15th of may 2003.

Done at Addis Ababa
This 15th day of May 2003,

# አባሪ1
## የከተማ አማካሪ ምክር ቤት አባላት ዝርዝር እና ብዛት

| ተ.ቁ | አባላት | የሥራ ድርሻ | ብዛት |
|---|---|---|---|
| 1 | የከተማው ከንቲባ | ሰብሳቢ | 1 |
| 2 | የካቢኒ አባላት | አባል | 9 |
| 3 | የከተማ ሥራ አስኪጅ | አባል | 1 |
| 4 | የከተማ ምክትል ሥራ አስኪጅ | አባል | 1 |
| 5 | ምክትል የቢሮ ኃላፊዎች | አባል | 7 |
| 6 | የከተማው አስተዳደር መሥሪያ ቤቶች ኃላፊዎች | አባል | 8 |
| 7 | የክፍለ ከተማው ዋና ሥራ አስኪያጅ ምክትል ዋና ሥራ አስፈፃሚ እና ቋሚ ኮሚቴ | አባል | |
| 8 | ከየቀበሌው ሁለት የነዋሪዎች ተወካይ | አባል | 480 |
| 9 | የቀበሌ ቋሚ ኮሚቴ | አባል | 30 |
| 10 | የከተማ ሴቶቸ ማህበር | አባል | 50 |
| 11 | የከተማ ወጣቶች ማህበር | አባል | 50 |
| 12 | የሠራተኛ ማህበር | አባል | 20 |
| 13 | የአዲስ አበባ ንግድ ምክር ቤት | አባል | 15 |
| 14 | የኢትዮጵያ አምራች ኢንዱስትሪ ባለቤቶች ማህበር | አባል | 10 |
| 15 | መምህራን ማህበር | አባል | 10 |
| 16 | የሙያ ማህበራት | አባል | 10 |
| 17 | አርበኞች ማህበር | አባል | 5 |
| 18 | የሲቪል ኅብረተሰብ ማህበራት | አባል | 10 |
| 19 | ዩንቨርስቲና የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት | አባል | 5 |
| 20 | የጤና ባለሙያዎች ማህበር | አባል | 6 |
| 21 | መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች | አባል | 10 |
| | | ድምር | |

# አባሪ 2
## የከተማ አማካሪ ምክር ቤት አባላት ዝርዝር እና ብዛት

| ተ.ቁ | አባላት | የሥራ ድርሻ | ብዛት |
|---|---|---|---|
| 1 | የክፍለ ከተማው ዋና ስራ አስፈፃሚ | ሰብሳቢ | 1 |
| 2 | የክፍለ ከተማ ቋሚ ኮሚቴ | አባል | 1 |
| 3 | ከየቀበሌው ሃያ ነዋሪ ተወካዮቸ | አባል | 3፥ እንደ ቀበሌው ብዛት |
| 4 | ቀበሌ ቋሚ ኮሚቴ | አባል | 5 |
| 5 | የክፍለ ከተማ መሥሪያ ቤቶች ኃላፊዎች | አባል | 30 |
| 6 | የክፍለ ከተማ ሴቶች ማህበር ተወካዮች | አባል | 20 |
| 7 | የክፍለ ከተማ ወጣቶች ማህበር | አባል | 20 |
| 8 | የክፍለ ከተማው መምህራን ማህበር | አባል | 10 |
| 9 | የአዲስ አበባ ንግድ ምክር ቤት | አባል | 10 |
| 10 | የሲቪል ህብረተሰብ ማህበራት | አባል | 20 |
| 11 | መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች | አባል | 10 |
| | | ድምር | |

# ANNEX 1
## List and number of City Advisory Council

| S.N | Members | Position | Number of Representatives |
|---|---|---|---|
| 1 | The Mayor | Chairperson | 1 |
| 2 | Members of the cabinet | Members | 9 |
| 3 | City Manager | Members | 1 |
| 4 | Deputy City Manager | Members | 1 |
| 5 | Deputy Heads Bureux | Members | 2 |
| 6 | Heads of organs of the city Government | Members | 8 |
| 7 | Sub-City Chief Excutive, and Deputy Chief Excutive and Standing Committee | Members | |
| 8 | Two reperesentative of resedents of each Qebele | Members | 480 |
| 9 | Qebele standing Committee | Members | 30 |
| 10 | City level Assosiation of Women | Members | 50 |
| 11 | City level Association of the Yputh | Members | 50 |
| 12 | Labour Union | Members | 20 |
| 13 | Addiss Ababa chamber of Commerce | Members | 15 |
| 14 | Ethiopian Manufacturing Industries Owners Association | Members | 10 |
| 15 | Association of Teachers | Members | 10 |
| 16 | Proffessionals Association | Members | 10 |
| 17 | The patriots Association | Members | 5 |
| 18 | Civil Associations | Members | 10 |
| 19 | University and Institution of Higher Education | Members | 5 |
| 20 | Health professional Association | Members | 6 |
| 21 | Non Governmentals organizations | Members | 10 |
| | | Total | |

# ANNEX 2
## List and number of City Advisory Council

| S.N | Members | Position | Number of Representatives |
|---|---|---|---|
| 1 | Sub-City Chief Excutive | Chairperson | 1 |
| 2 | Qebele standing Committee | Members | 1 |
| 3 | Twenty Respresentativs of residents from each Qebele | Members | 3X NO of Qebele |
| 4 | Standing Committee of Qebele | Members | 5 |
| 5 | Heads of Sub- city Government Office | Members | 30 |
| 6 | Sub-City Assosiation of women | Members | 20 |
| 7 | Sub-City Assosiation of Youth | Members | 20 |
| 8 | Sub-City Assosiation ofTeachers | Members | 10 |
| 9 | Addis Ababa Chamber of Commerce | Members | 10 |
| 10 | Civil Societies | Members | 20 |
| 11 | Now-Government Organizations | Members | 10 |

| | |
|---|---|
| Total | 489 |

## አባሪ 3
## የቀበሌ አማካሪ ምክር ቤት አባላት ዝርዝር

| ተ.ቁ | አባላት | የሥራ ድርሻ | ብዛት |
|---|---|---|---|
| 1 | የቀበሌ ዋና ሥራ አስፈፃሚ | ሰብሳቢ | 1 |
| 2 | የቀበሌ ቋሚ ኮሚቴ | አባል | 5 |
| 3 | የቀበሌ ነዋሪ ተወካዮች | አባል | ከ300-400 |
| 4 | የሴቶች ማህበር ተወካዮች | አባል | 20 |
| 5 | የወጣቶች ማህበር ተወካዮች | አባል | 40 |
| 6 | መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች | አባል | 10 |
| 7 | የመምህራን ተወካዮች | አባል | 20 |
| 8 | የሕክምና ባለሙያዎች ተወካዮች | አባል | 10 |
| 9 | የቀበሌ የትምህርት ዴስክ | አባል | 15 |
| 10 | የቀበሌ የትምህርት አመራር ተወካዮች | አባል | 20 |
| 11 | የሲቪል ህብረተሰብ ማህበራት | አባል | 15 |
| 12 | የአካባቢ ልማት ማህበር | አባል | 20 |
| 13 | የእድር አመራሮች | አባል | የሁሉም እድሮች |
| 14 | የቀበሌ የልማት ኮሚቴ | አባል | |
| | | ድምር | እስከ700 |

## ANNEX 3
## List and number of City Advisory Council

| S.N | Members | Position | Number of Representatives |
|---|---|---|---|
| 1 | Qebele Chief Excutive | Chairperson | 1 |
| 2 | Qebele standing Committee | Members | 5 |
| 3 | Respresentativs of Qebele residents | Members | 300-400 |
| 4 | Respresentativs as the Assosiation of women | Members | 20 |
| 5 | Respresentativs Assosiation of youth | Members | 40 |
| 6 | Now-Government Organizations | Members | 10 |
| 7 | Respresentativs of Teachers Association | Members | 20 |
| 8 | Respresentativs of Health Proffestionals Association | Members | 10 |
| 9 | Qebele Education Dsk | Members | 15 |
| 10 | Respresentatives of Qebele Education Management | Members | 20 |
| 11 | Civil Societies | Members | 15 |
| 12 | Local Development Association | Members | 20 |
| 13 | ``Edire`` Leaders | Members | All |
| 14 | Qebele Development Committee | Members | |